# የሚያሳዝኑና የሚታዘንባቸው በዙሳ?

ገመቹ አበበ

ወደ ረግረጉ ሁለት ዓይኔን ከፍቼ ጥልቅ እያልኩ መሆኑ አልጠፋኝም። ድፍረቱን ያገኘሁት ስንዝሮ ፖለቲከኞች ብሎ ከጻፈው ወንድሜ ነው። የታጠቀ አገዛዝን እንጋፈጣለን እየተባለ የምንፈራቸው እንቶኔዎች ሊኖሩ አይገባም። የሕዝብ ጎራ በር አጥር አልባ መስኋቸው ዘው ብለው ገብተው የሚወዛወዙ እየፈጠሩ ያሉትን አሳዛኝ ሁኔታ በዝምታ ልናይ የሀገራችን ቀውስ አዘል ሁኔታ የሚፈቅድልን አይደለም። ልሂቆቹን፣ መሪ የሚባሉትን፣ ዘመናዊ ደጃዝማቾችን ደፈራችሁ ባዮች ሊቃወሙ መቻላቸው ግልጽ ነው። ታዲያ ማን ይፈራልና ነው ጫጫታና ጩኸት !?

በጣም የሚያሳዝኑ ሁለት ነፍሳት ወደ ወያኔ ፓርላማ የገቡት የመድረክና የመኢአድ ተመራጮች ናቸው። 544 ወያኔ መሀል ሁለቱ ዓይናቸውን ሲያቁለጨልጩ ይታዩኛል። የተቃዋሚ ድርጅቶችን ስህተትና ክስረት ጠቋሚ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ ግለስቦቹ ግን ሊታዘንላቸው ይገባል። የሚታዘንባችው ሊባሉ ከሚችሉት ደግሞ የመጀመሪያው የመለስ ተቃዋሚ ተብሎ የሚነገርለትና ለመጪው አምስት ዓምት ምርጫ እንዘጋጅ ሲል የተደመጠው ስዬ አብርሀ ነው። ይህ ሰው ለከዚህ በፊቱ ከባድ ጥፋቱ ምንም ይቅር በሉኝ ሳያሰማ የሕዝብ መሪ ነኝ ብሎ የተሰየመ ነው። ተልእኮው የገማ የገለማውን ዘረኛ የወያኔ ስርዓት መለስን ቀንሶ ለመቀጠል ነው የተባለ ሲሆን በወያኔ ምርጫ መሳተፍ ውድቅነቱ ከተረጋገጠም በኋላ ለምርጫ እንዘጋጅ ጥሪው ወያኔን ለመጥቀምና ትጥቅ ትግልን ለማደናቀፍ ነው መባሉ  ስህተት አይደለም። ይታዘንበታል። ዛሬም ይህን ግለሰብ መሪ ብለው ተቀብለው ለመቀጠል የቆረጡት ደግሞ የሚታዘንላችው ናቸው።  ይባስ ብለው ደግሞ ለውርደቱ ምርጫ ሰለባ የሆኑት ድርጅቶች ጥሩ ሰሩ ብለው የሚደርቁት በርግጥም አሳዛኝ ፍጡሮች ናቸው።

ሌላ ሊታዘንላችው የሚገባ ደግሞ አዛውንቱ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ ናቸው። ምርጫ መግባትን ሲደግፉ ቆይተው አሳፋሪ ውጤቱ ሲታይ ደግሞ በቃ ክተት ነው የቀረን አማራጭ ሲሉ ቢዘገይም ሁኔታውን ተረዱ ብለን ተደስተን ሳናበቃ ለአዲስ ድምጽ ራዲዮ አዘጋጅ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ደግም በሚያስገርም ሁኔታ ክተቱ ወያኔንም ይጠቅልላል ብለው ኣሳፈሩን። ክተት በጠላት ላይ የሚወስድ አቅዋም ሲሆን የክተቱ አካል ራሱ ጠላት መባል ያለበት ከሆነ ደግሞ ነገሮች ለጠሪው ተደበላልቀዋል ማለት ነው። ፕሮፌሰሩ የፖለቲካ ነገረ ውሉ እያመለጣችው ለመሆኑ ሌላ መረጃ ሲሆን የ 15 ሰው ኮሚቴ አቋቁመን ይህ ኮሚቴ ባሻውና በወሰነው ለሚታገሉ ድርጅቶች (እነዚህ እነማን መሆናቸውንም ይህ ተዓምራዊ

ኮሚቴ በራሱ ወስኖ) የተዋጣ ገንዘብን አዳይ ይሆናል ያሉት ነው። ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ የተባለው ዓይነት ሆኗል የሳቸው ነገር!

የሚያሳዝኑ ስንል በምጸት ወይም በሽሙጥ መሆኑ ድብቅ አይደለም። ሐሳዊ መሲሆችንና አስመሳይ ነጻ አውጪዎችንም አምነው የሚባክኑት ደግሞ ቢነገሩም አልሰማ ያሉ በመሆናችው የሚታዘንላቸው ሳይሆኑ የሚታዘንባቸው ቢሆኑ ሊያስገርም አይገባም። መለስ ዜናዊ ተጠቅሞባቸው ዛሬ ሊያራግፋችው ለወሰነባቸው ለነ ስዩም፤ አዲሱ፤ በረከት ወዘተ የሚያዝን ካለ የሚታዘንበት ይሆናል። የዳዊት ዮሐንስን ክፉ ዕጣ ይስጣቸው ማለቱ ሲያንስ ነው።

- የቡግና ሕዝብ ጠራኝ ብሎ ሄዶ ሽንፈትን የተከናነበውና አሁንም በክህደቱ ቀጥሎ ለመጪው ምርጫ እንዘጋጅ የሚለው፣
- ስዬ በተምቤን፤ አረጋሽ በአድዋ፤ ገብሩ በመቀሌ ሲያሽንፉ የታያቸው፣
- ወያኔ በምርጫው ቢያሽንፍ ወይም ቢያጭበረብር ሕዝብ ሆ ብሎ ተነስቶ ይጥለዋል ያሉን፣
- ያው የፓርላማ በርጩማማ እንነፈግም ብለው ያመኑት እነ በየነ ጴጥሮስ፣
- ከወያኔ አገዛዝ ጋር በሰላም አብሮ መኖርን የስበኩንና ወደዚያውም ሊጓዙ ተነስተው የነበሩት ሁሉ ዛሬ ኩም ቢሉ ወይም አልሆን ቢላቸው ልናዝን መቸም መጠበቅ የለበትም።

ሌላም አንድ ድንቅ የሚለኝ ነገር አለ። የተለያየ ዓላማና ግብ ያውም የሚቃረን ያላቸውም ቢሆኑ አብረው ወያኔን ለመጣል መነሳት አለባቸውም የሚሉም አሉ። በተለይ ከሰሞኑ። የትግሉ የመጨረሻ ግብ ወያኔን መጣል ብቻ የሆነ ይመስል። እያንዳንዱ ድርጅት ወያኔን ለመጣል ሲዘጋጅ የየራሱን ግብ ሰንቆ ነው። አብሮም ወደዚያ መዳረሻ ግብ የሚያደርሰውን የቤት ስራ እግረ-መንገዱን እየሰራ። ወያኔን መጣል - የሚታገለው ወገን ወደሰነቀው ግብ የሚወስድ የትግሉ መዳረሻ መንገድ ይመስለኛል። በራሱ ግን የመጨረሻ ግብ አይመስለኝም። ለዚህም ደግሞ ድርጅቶቹ በዓላማቸው ስር አሳምነው የሚያሳባስቧቸውን ታጋዮች ይከፍሉ ዘንድ የሚጠይቋቸው ውድ ሕይወትንም ይሆናል። ወያኔ ከወደቀ በሁዋላ ስለሚከተለውና ስለሚደረስበት ግብ/ውጤትም የሚያስጨብጧቸው ህልም ይኖራል። አለዚያማ መድረሻውን የማያውቅ መንገደኛ ቢጤ ይሆናሉ።
ታዲያ በኢትዮጵያ አንድነት ስር የሁሉም እኩልነት መረጋገጥ አለበት፣ ከቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት «አብስኒያውያንን» በተገኙበት ሌላው ቀርቶ በውጭም ያለን ኀረቤት መጠራረግ አለብን፣ ወያኔ በየአምስት ዓመቱ በሚያካሂደው የቧልት ምርጫ የሚቸረንን ወንበር እየለቃቀምን በተስፋ ለማሸነፍ እንጠብቅ፣ የሀገርና የሕዝብ ህልውና ሳይጠፋ በመሳሪያ

ታግለን እናስወግደው፣ ወያኔን እንደማንኛውም የስልጣን ተፎካካሪ እንጂ እንዴ ጠላት አንየው ወዘተ የሚሉት እንዴት ነው ተቀናጅተው የሰመረ ትግል ሊያካሂዱ የሚችሉት? ወያኔንም ጨምሮ ትግላችንን ለማኮላሸት በሚፈልጉ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይሎች የሚገፉትን ወይም በራሳቸው ግላዊ አለዚያም ጠባብ ቡድናዊ ጥቅም ተነሳስተው ትግሉን ንግድ ያደረጉትን አስመሳይ ተቃዋሚ እንዴት ከእውነተኞቹ የምንለያቸው? ለዚህ የመጨረሻ ጥያቄዬ መቼም መልሱ ወያኔን ከጣልን በሁዋላ የሚል እንዴማይሆን ግልፅ ነው። ምነው ቢሉ እነኝህ ወያኔ ወይም ባዕድ ተከል አስመሳይ ተቃዋሚዎቹ እኮ ዋና ስራቸው የወያኔን እድሜ ለማራዘም፣ ትግሉን ማኮላሸት ነው። ለዚህ ደግሞ በትምህርትነት ያሳለፍናቸውን ሃያ ዓመታት ወደሁዋላ መመርመሩ ጠቃሚ ነው። አለዚያ አንደኛቸው ትዳራቸውን ለማፍረስ፣ ሌላው ለማጠናከር የቆረጡ ባልና ሚስትን እንደየዓላማችሁ እየሰራችሁ አብራችሁ ኑሩ እንደሚል ሽማግሌ መሆን ነው። ማፍረስና መገንባት የሚቃረኑ ናቸውና። እርስ በርስ የሚጣላለፍ ስብስብ ፈጥረን የወያኔን ዕድሜ ማራዘም ካልፈለግን በስተቀር። ሌሎችም ብዙ ጥያቄዎችን ያጭራል - ይህ ተቃዋሚዎች የተባሉ ሁሉ በጅምላ ይተባበሩ የሚለው ጥሪ።

የምንታገለው እኮ ካፍ እስከጢሙ የታጠቀ፣ የሀገሪቱን ሀብት ተቆጣጥሮና በባዕዳን ጌቶቹ እሽሩሩ እየተባለ በድርጅታዊ የስለላ እና የእመቃ ሃይል የተጠናከረ አገዛዝ ነው። በኢትዮጵያ መቃብር ላይ ትግራይ ትግርኝን እመሰርታለሁ ብሎ ደደቢት በረሃ ላይ የተወለደና ለዚህም ግቡ መሳካት እስካሁን ግንባሩን ሳያጥፍ የሚሰራ ወንዙ የደረቀበት ሰይጣን። በአጭሩ ካላጠፉት የሚያጠፋ ፀረ-ኢትዮጵያ ሃይል ነው ወያኔ።

ይህ ከሆነ ደግሞ የሚታገለው ተቃዋሚ ሃይል ያሸንፈው ዘንድ በአንፃሩ ጠንካራ መሆን አለበት። ከብረት የጠነከረ የዓላማ አንድነትና መተማመን፣ ንፋስ የማይገባበት ድርጅታዊ ስምረት፣ አቅምና አሰራር ያሻዋል።

እናም እነኝህን ግራ አጋቢ አሳዛኞች ግን በቃችሁ! አታደናቁሩን! ውጤት አልባ በሆነው ሆያ ሆያችሁ የትግሉ አርሾ የሚሆኑ ወገኖቻችንን በከንቱ በወያኔ አታስበሉ ሊባሉ ይገባል ። በሕዝባችንም የትግል ሞራል ላይ የአዞ እንባ አፍሳሽ አትሁኑ ልንላቸው። እኛም ቀበቶቻችንን ጠበቅ አድርገን የማይቀረውን አማራጭ መንገድ መያዝ አለብን - ወያኔንና አጋሮቹን በሚገባቸው የትግል ቋንቋ ማነጋገር - በትጥቅ መፋለምን ያካተተ ሁለገብ ትግል። ለዚህ ደግሞ በግለሰብም ሆነ በድርጅት ደረጃ ወያኔንን ከጠላትነት ለመፈረጅ ልባቸውን ባር ባር የማይላቸው የአንድነት ሃይሎች ትግላቸውን ለማቀናጀት ወቅቱ አሁን ይመስለኛል። የወያኔና የተስፋ አስቆራጭ ቱልቱላዎቹ የገደል ማሚቶ ሆነን መላውን ተቃዋሚ እየተቸን የዳር ተመልካች ከመሆን ይልቅ ጥሬውን ከብስሉ፣ የመርህ ቱሪስቱን ከፅኑው፣ ለስላሴውን ከመራሩ ፈዋሽ እንቆቅ እየለየን የአንድነት ሃይሎችን ድርጅታዊ እንቅስቃሴ እናጠናክር።